# *ብቻኛው መንገድ*

**ከ ቆልፊው**

ትናንትና ችግር፡ ዛሬ ችግር፡ ነገም ችግር ስናወራ ግን መንስኤ ሳንሰጥ ለሌላ ወሬ በመዘጋጀት ላይ ያለን ይመስላል::**አዲስ ድርጅት አዲስ ትግል**:: ችግራችንን ማብራራት ሳይሆን ችግሩን ከመቅረፉ ላይ ነው ዋነኛው ትኩረታችን መሆን ያለበት:: ስለ ምርጫው መጭበርበር አውርተን ሳናበቃ ሌላኛው ምርጫ መጥቶ አልፏል:: ዋነኛውም ምርጫ ሳይመኙት በፍጥነት በመምጣት ላይ ነው:: አንወዳደርም ያሉት ወሬው ለዜና ከመቅረቡ በፊት ተመራጭ ሆነው የቀረቡበት ሁኔታ አይተናል:: የመሳሪያ ትግልን የረገሙ ዛሬ ያለመሳሪያ ትግል . . . ሲሉ መስማቱ ከማስገረምም አልፎ ከምራቸው ነውንን ብለን ሳንጠይቅ አልቀረንም:: መሳሳት ያለ ነው:: **እጅግ በጣም አስቀያሚው ግን ከስህተት ያለመማሩና ስህተትን አለመቅረፉ ነው::**

ያለፈውን ስህተት መመርመሩ ለዛሬ የሚበጀንን መላ ለማግኘት ያስችለናል:: የዛሬው መልካም ተግባራችን ደግሞ ለነገው መንገዳችን ብርሃን ይሰጠናል:: ስለ ዛሬው ወያኔ ስንገመግም ያለፉትን የብዙ ሽህ አመታት ታሪካችንን እየቃኘንና እያደነቅን ስለመሆኑ ይገባኛል:: የዛሬውን የወያኔ መንግስት ክፉ ተግርባር እየተገነዘብን የነገዋን ብርቅዬ ኢትዮጵያ ከውያኔ በሽታ የጸዳች አድርጎ ለመገንባት እየተረባረብን እንዳለን ተስፋ አደርጋለሁ::

የሆነ ሆኖ ትላንትናና ዛሬ አየሰራነው ያለው ስህተት ከጠላት የመነጨ ሳይሆን ከራሳችን ከተቃዋሚ ተብዬዎቹ መሆኑን አስረግጬ መናገር እወዳለሁ:: የተቃዋሚው ጎራ ሌት ተቀን የሚደክመው ከወዳጁ ጋር በመታገል ነው:: አንደኛው ትግል ሲያልቅ ሌላ የምንታገልበት አጀንዳ ይቀረጻል:: ያለፈውን ሁላችንም የምናውቀው በመሆኑ ለጊዜው ተወት አድርገን ባሁኑ ወቅት ተቃዋሚው ወገን ምን እያደረገ ነው የሚለውን ጥያቄ ማጤኑ የሚበጅ ይሆናል:: አጀንዳችን ካለው የኢትዮጵያ ችግር ላይ ያነጣጠረ ነው ወይስ እንደትናንቱ የርስ በርስ መጠላለፍ ላይ ያተኮሩ ነው? ያለፈው ትግል ፍሬው የመከነው ወዳጆችን የመረዘው ወረርሺን በሽታ እርስ በርሳችን እያላጋን በመቆየቱ ነበር:: ወረርሽኙ መጥፋቱን የሚያሳምን እንዳችም ፈዋሽ መድሃኒት ባለማየቴ በዚያው ጭለማ ውስጥ እየተንዝ ነን ያለነው ብዬ ባስብ አትቀየሙኝ::

ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅት በሽተኛ ነው ማለት አይደለም:: ህይወታቸውን ጉልበታቸውን ገንዘባቸውንና ቤተሰባቸውን የሰው በርካታ የተቃዋሚው ድርጅት አባላት ስለመኖራቸው መካድ ተገቢ አይሆንም:: ላለቋት አርባ አመታት የታገሉ አሉ አሁንም በትግሉ መስክ:: ሁልት ሶስት አመታትም ያስቆጠሩ ግን ያርባ አመት ያህል የጎዱንም አሉ:: ተመክሮም መናኛ የሆነበት ዘመን ላይ በመድረሳችን ሊከፋን የሚገባ ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን ብንኖርም የሚገርም አይደለም:: በሌላ ወገን ግን የያዙት የማጭበርበር የትግል ዘዴ አልሰራ ሲላቸው **ድርጅታዊ ቆዳቸውን እንደ እባብ ሲገሽልጡ** የምናያቸውን ድርጅቶች ወይም መሪዎቻቸውን ማጋለጠ ስለኢትዮጵያ እንቆረቆራለን ለምንለው ሁሉ የሚጠበቅብን ግዴታችንም ነው:: ከወያኔ ጋር መስራት ይቻላል ባዩ ጉደኛው የዘንድሮው የኢሕአፓ እንጃና ባንጃነት ላለመጠራት በመፍራቱ ከቅንጅት ወጣሁ ባዩ ክንፍ በቅርቡ አዲስ ድርጅት

ፈጥሮ አዋጅ ለማሰማት ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶናል። ገና ድርጅት ሳይኖረውም  የትጥቅ ትግል እያካሄደ ነው የሚል ሃሜት በማስወራት ላይ ነው።

የነገዋን ኢትዮጵያ ለማቆየት የዛሬዋን ኢትዮጵያ መንከባከብ ግዴታችን ነው። ዛሬ ለኢትዮጵያችን የሚሻት የድርጅት ብዛት አይደለም። ሃገርን ለማዳን ባንድነት መታገሉ እንጅ ወሳኙ የድርጅት ብዛት አይደልም። አንድ ራሱን ብቻ ሆኖ ባለድርጅት የሆኑ ድርጅት ባይ ነን የሚሉ መኖራቸው አዲ ዜና አይደልም። ከነስማቸውና ከነድርጅት መጥቀሱ ይቻላል። ሙከራቸው ለሃገር እስከሆን ድረስ ቢበረታቱም የተቃዋሚውን ጎራ የሚያሳብጡ ፊኛዎች በመሆናቸው ቶሎ ሊተነፍሱ ስለሚችሉ ድርጅታዎ ምኞታቸውን ትተው  ላገር ሲሉ ከሚደግፉትና አባላት ካላቸው ድርጅቶች ቢጠጉ ይመከራሉ። የህብረቱንና የቅንጅትን ቀፎ ብንከፍተው ብዙ ጉድ የሚነግረን  መረጃ ማግኘት ይቻላል። ዛሬ ቅንጅቱና ህብረቱ ያሉበትን ሁኔታ ስናየው መሳቅ ወይስ ማልቀስ ነው ምርጫችን? ያ ሁሉ ሚሊዮን ዶላር የተሰበሰብ የት ደረሰ?

የወቅቱ ጥያቄ አንድና አንድ ብቻ ነው። እሱም **ኢትዮጵያን ማዳንና ለመጭው ትውልድ ማስረከብ ነው**። ይህን ለማድረግ ደግሞ ወሳኙና ትኩረት መሆን ያለበት ወያኔን ከላያችን ማንሳቱ ነው። እኔ ልምራ ወይም የኔ ድርጅት ይበልጣል ማለቱ የውያኔን ዕድሜ ከማራዘሙ ባሻገር የኢትይዮጵያንን ሃገራዊ ህልውና ጥፋትን ማገዝ ይሆናል።ወያኔን ለማውረድና ኢትዮጵያን ለማዳን ደግሞ አንጃ መሆን ወይም አዲስ ድርጅት መቀፍቀፍ በፍጹም የሚመረጥ መላ ከቶም ሊሆን አይችልም። በየቀኑ ድርጅት መፍጠር የድክመት ነጸብራቅ የሚጠቁም እንጂ የጥንካሬ መግለጫ አይደለም። ራሳቸውን ያላሳወቁ ስንት ድርጅቶች እንዳሉ ባናውቅም በሚቀጥለው ሳምንት ከንቲባ ብርሃኑ አዲሱን ድርጅታቸውን ሊያሳውቁን አኮብኩበዋል። ተተባበቁም አስብለዋል። ይቅናቸው። መብታቸውም ነው። የኢሕአፓውስ አንጃ ከእስር ተለቀቅን ብለው በመውጣት ህዝቡ ድንቅ የሚሏቸው መስሎአቸው አልነበረምን? የኢትዮጵያን ችግር ለመቅረፍ መፍትሄው ድርጅት ማራባት አይደልም። እንጃ ማበራከትም አይደለም መትሄው። እነሱ እንኳ ይህን ያጡታል ብዬ መድከም የለብኝም። ብዙሃኑ ግን በቂ መረጃ ስለሌለው በቀላሉ ሊያወናብዱት  ስለሚችሉ ግንዛቤ መስጠቱ የግድ ይላል።

ሌላ ሊባል የሚገባው ሃቅ ለኢትዮጵያ የሚሆን መፍትሄ ማምጣት የሚችለው ውውጭ ያለነው ህዝብ  ሳይሆን በምድረ ኢትዮጵያ ኗሪ የሆነው ህዝቧ ስለመሆኑ አጥብቆ  መነገር ያለበት ሃቅ ነው። በዲያስፖራ ያለው ወገን ጥቅም አይሰጥም አላልኩም። የራሱ የሆነ ግን እጅግ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የሆነ አስተዋጽዎ በዲያስፖራ ኗሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ ጠቀሜታ ሳልረዳው ቀርቼ አይደልም። የሆነ ሆኖ ግን ወሳኙ ባገር ቤት ያለው ኢትዮጵያዊ ስለመሆኑ ሁላችንም ልናምነው የሚገብ ሃቅ ነው። አለን የሚሉ ድርጅቶች በሙሉ ዋነኛውን እንቅስቃሴያቸውን ማካሄድ የሚገባቸው ባገር ቤት ላይ ነው። እዚህ ዲሲ ተራራ ላይ ተቀምጠን ወያኔን ለመቀየር ቀርቶ ለማስድንገጥ አይቻልም ከንቲባ ብርሃኑ የሚሰሙኝ ከሆነ?

ሌላው ሁሌ የሚያበሳጨኝ ጉዳይ የሃይማኖት መሪዎች ስለሃገር ማውራት ፖለቲካ ወይም ኮረንቲ አድርገው ማየታቸው፡ ነው። አጼ ምንሊክ ታቦት ይዘው ነው እኮ አደዋ የዘመቱት። የሃይማኖት መሪዎችና ራሱ ሃይማኖት ስለ ጭቁኑና ምስኪኑ ህዝብ  መብት መቆርቆር ካልቻሉ ምንድነው ተልእኳቸው? ሃይማኖቶች ስለ ሃገራቸው ካላወሩ ካልተቆረቆሩ ምን ይሆን ስራቸው? ነብዩ መሃመድ ሆነ እየሱስ ስለ ምስኪኑ አስተምረዋል። ስለ በዳይ ገዥዎችም ተገቢ ያልሆን ባህሪያቸውም ሰብከዋ። ***ሃብታም መንግስተሰማይ ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ መሽልኳ ይቀላልም*** ል ተብሎ መስርበኩንም አውቃለሁ። የሃይማኖት መሪዎች ስለጭቁኑ ሰቆቃ ተናገሩ። ያለውን መንግስት እርገሙት። ፈጣሪ ጸሎታችሁን

ይሰማልና ሌባውን ሌብ፡ አምባገነኑንም አውግዙት፡፡ ይህን ካላደረጋችሁ ግን በመሬት የምእመናት በሰማይ የመላእክታትን **መርገም መርገም** ለመሸከም ተዘጋጁ፡፡

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ በምእራብ ኢትዮጵያችን ያለው ድንበራችን ተፈትኗል፡፡ ህዝባችን ተገድሏል፡፡ ወገናችንም ለእስራት ወደ ሱዳን ተግዟል፡፡ ይህን እያየነ ዝም አንልም፡፡ ግን የዚህን አካባቢ ሰቆቃ በመጠቀም የግል ዝናን ለማንገስንና ኪሱን ለማደለብ ከጎመዠ ድርጅት መጠንቀቅ እንደሚገባን በቅድድሚያ ነቅተን ዘብ በመቆሙ ማመን የወግ ነው፡፡ ያለኔ ድርጅት ላፈር ያሉ ድርጅቶች ምንኛ ኪሳችንን አቅጥነው የነሱን ኪስ ማደለባቸውን ዛሬ ሳስበው ይቆጨኛል፡፡ ዳግም ላለመጭበርበር ወገን ንቃ!!!

በመጨረሻ አንድ ማለት የምፈልገው ቁም ነገር ሰሞኑን በኢህአፓ ስለ ስለተላለፈው ጥሪ ነው፡፡ ሃገረን እወዳለሁ የሚል፡ ድርጅቴ የቆመው ላገር ነው የሚል የፖለቲካ ድርጅት፡ ሃይማኖቴን አከብራለሁ የሚል የዕምነት ድርጅትና፡ እንዲሁም ሃገሬ ናት ክብሬ የሚለው ወገን ሁሉ ለጥሪው ምላሽ ባስቸኳይ መስጠት አለበት፡፡ ለትሪው ምላሽ መስጠት ሳይሆን ዋናው ቁምነገሩ ተግባራዊ የሆነ አስተዋጽኦ ከማበርከቱም ላይ ነው፡፡ አንድና ሁለት አባላት ይዞ ድርጅት ነኝ የተባለበት ዘመን አብቅቷል፡፡ ለኢትዮጵያ ችግር ምላሽ ሰጭ ድርጅት ጥርስ ያለው መሆን አለበት፡፡ የሞቅ ሞቅ ትግሉም ማብቃት እንዳለበትም ለከንቲባ ብርሃኑ መነገር ካለበትና የሚገባውም ከሆነ ሳንፈራ እንንገረው፡፡

ወያኔንን ለማውረድ ብቸኛ መንገዱ ወያኔን መታገል ብቻ ነው!!!
በህዝባችን ቆራጥ ተጋድሎ ኢትዮጵያችንን እናድን!!!
ለኢሕአፓ ጥሪ ፈጣን ምላሽ እንስጥ!!!